# Learning by Ear 2013

መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ -ከባድ አማራጮችን መጋፈጥ

EPISODE TWENTY-FOUR: **የቤተሰብ ቅልቅል**

**AUTHOR: Chrispin Mwakideu**

**EDITOR: Madelaine Meier, Ludger Schadomsky**

**COPY EDITOR: Charlotte Collins**

**List of characters by scene:**

**SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት IN ትዕግስት 'S BEDROOM**

- ምህረት (F, 15)
- ትዕግስት (F, 15)

**SCENE 2: ቅዱስ , ብሩክ AND አቶ ደንበል ARRIVE IN TANDIKA**

- አቶ ደንበል (M, 40)
- ብሩክ (M, 8)
- ቅዱስ (M, 8)

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND አቶ ሙላቱ ARRIVE IN THE CITY**

- ወ/ሮ ሉሊት (F, 40)
- አቶ ሙላቱ (M, 45)
- ቅዱስ (M, 8)
- ብሩክ (M, 8)

## SCENE 4: ምህረት TAKES A PREGNANCY TEST

- ትዕግስት (F, 15)
- ምህረት (F, 15)
- ዶክተር ዘሪሁን (M, 45)

## 1. INTRO - NARRATOR:

ጤና ይስጥልን አድማጮች ይህ "መንታ መንገድ ላይ ያለ ትውልድ" በሚል ርዕስ የሚቀርብላችሁ የበማድመጥ መማር ድራማ ነዉ። 24ኛው ክፍል ላይ ደርሰናል። እስቲ መለስ ብለን የሆኑትን ነገሮች እንቃኝ።:

አቶ ሙላቱ ተቀጥረው ይሰሩበት የነበሩበት ቤት በዘረፋ ወንጀል ተጠርጥረዋል። ይሁንና የባለቤቱ የአቶ ጃለታ ልጅ ንጉሴ ምህረትን ማለትም የአቶ ሙላቱን ልጅ በጊዜ ስላስጠነቀቀ አቶ ሙላቱ ከፖሊስ ሊያመልጡ ችለዋል። ጉዞዋቸውም ወደ ባለቤታቸው ወ/ሮ ሉሊት ወላጆች ቤት ወደ ገጠር ነበር። ወ/ሮ ሉሊት ከባለቤታቸው ከተጣሉ በኋላ ኑሯቸውን ከወላጆቻቸው ጋ እንዳደረጉ የሚታወስ ነው።

2. **ወ/ሮ ሉሊት (EP 22, 75):** "ሙላቱ? ከየት ነው የምትመጣው። ምህረት የታለች? ለምንድን ነው ብቻህን የመጣኸው?"

3. **LIPI:** "ሙላቱ፤ እዚህ ምንታደርጋለህ? አንተ ሰካራም።

4. **ወ/ሮ ሉሊት:** "ቆይ እማ ! እኔ አነጋግረዋለሁ።" **(+85)** "እሺ ሙላቱ። ምንድን ነው ልትነግረኝ የፈለከው?"

አቶ ሙላቱ ከባለቤታቸው ከተጣሉ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ ተገናኝተዋል። ይታረቁ ይሆን? መቼ ይሆን ሁለቱ መንታ ልጆቻቸው ወደቤት መንገድ እንደጀመሩ የሚያውቁት? በዛሬው ጭውውት እንደርስበታለን። ከዛ በፊት ግን ምህረት ለጓደኛዋ ትዕግስት ባለፈው ክፍል የነገረቻትን ሚስጥር አስታውሱ

5. ትዕግስት (EP 23, 117): "ግን – ምህረት በዚህ ወር የወር አበባሽ መጥቶ ነበር አይደል?"

6. ምህረት : "አልመጣም… እሱን እኮ ነው የምልሽ – ዘግይቷል።"

7. ትዕግስት : "ወይ ጉድ!"

ምህረት ከክፍል ጓደኛዋ ዳንኤል ጋ የግብረ ስጋ ግንኙነት ፈፅማ ነበር። እና አሁን ችግር ላይ ትወድቅ ይሆን ወይንስ እንደው ዝም ብላ ነው የምትሰጋው? የዛሬውን « የቤተሰብ ቅልቅል» የተሰኘውን ክፍል ምህረትን እና ትዕግስትን ከተውናቸው መኝታ ቤት ውስጥ እንዳሉ ስናገኛቸው ነው የሚጀምረው።

## SCENE 1: ምህረት AND ትዕግስት IN ትዕግስት 'S BEDROOM

8. SFX: BAG BEING DROPPED DOWN

9. ምህረት: (terrified) ወይጉድ? ምንድን ነው የምትይው፤ ጉድ?

10. ትዕግስት : እንግዲህ ከዳንኤል ጋ እንዳደረጋችሁ ነግረሽኛል አይደለም እንዴ?

11. ምህረት : (worried) አዎን ግን በጣም ቶሎ ነው ያበቃው

12. ትዕግስት : መቼ የወር አበባሽ እንደሚመጣ ከወር አበባ ቀን መቁጠርያሽ ላይ አመሳክረሻል?

13. ምህረት: (confused) ከወር አበባ ቀን መቁጠሪያ የሚባል ነገር አለ እንዴ? ስለዚህ ሰምቼም አላውቅ።

14. ትዕግስት : ወይኔ ምህረት … ምን አልባት ተሳስቼ ይሆናል ግን እርግዘሽ ሊሆን ይችላል።

15. ምህረት: (defensive) በኔ ላይ መቀለድሽን አቁሚ ትዕግስት። እርጉዝ ልሆን አልችልም። እንዴት? (fumbling with words) እኔ… እኛ… ማለቴ እኔ ደህና ነኝ።… እንዴት ልታውቂ ትችያለሽ?

**16.** ትዕግስት : እሱን እኮ ነው የምልሽ ምህረት። ትክክል ላልሆን እችላለሁ። ግን የወር አበባሽ ሳይመጣ ከቀረ እና ያለ ምንም መከላከያ ከሆነ ያደረጋችሁት … መቼም… አይሆንም ለማለት ይከብዳል። ቁጭ በይ ለማንኛውም …

**17. SFX: SOUND OF PERSON SITTING DOWN ON A BED**

**18.** ትዕግስት : ምህረት ይህን ለማረጋገጥ አንድ አማራጭ ነው ያለው።…

**19.** ምህረት **:** **(trying to argue with herself)** ግን እኔ ገና 15 አመቴ ነው። እርጉዝ ልሆን አልችልም። ይህ በፍፁም ሊሆን የማይችል ነው።

**KW BEGIN**

**20.** ትዕግስት : ምህረት ተረጋጊ። በመጀመሪያ ማድረግ የሚገባሽ ነገር ቢኖር ማርገዝ አለማርገዝሽን ማረጋገጥ ነው። አንዳንድ ጊዜ ፔሬድሽ ይዘገያል። እና ያ ትክክለኛ ያልሆነ ምልዕክት ነው። ዶክተራችንን ልጥራቸው እና እዚሁ ምርመራውን ሊያደርጉ ይችላሉ። ያኔ የበለጠ እናውቃለን።

**21.** ምህረት**:** **(nervous)** እውነትሽን ነው? እንግዲህ.. ሌላ ምን አማራጭ አለኝ። ግን ትዕግስት ምርመራው ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል? ቶሎ ማወቅ እፈልጋለሁ።

**22.** ትዕግስት : ስሚ ምህረት ፤ ላለመጨነቅ ሞክሪ። ቀላል ነው ዶክተሩ ሁሉንም ነገር ያብራራልናል። …

**23.** ምህረት**:** **(still lost in thought)** ወላጆቼን ምንድን ነው የምላቸው? አባቴ ይህን ቢያውቅ ይገለኛል። እናቴ ከሰውነት ውጪ ነው የምትሆነው… ርዕሰ መምህርቷ… ዘመዶቼ… የሚያውቁኝ ሰዎች ሁሉ…ስለእኔ ምን ያስቡ ይሆን?

**24.** ትዕግስት**:** **(shouts)** ምህረት፤ ለመሆኑ የምልሽን ነገር ሰምተሻል?

**25.** ምህረት: **(pleading)** ወደቤት መሄድ አልችልም ትዕግስት ። ከአቅሜ በላይ ነው። - ፖሊሶች አባቴን እያፈላለጉት ነው። እናቴ ትታው ሄዳለች። ስለ መንታ ወንድሞቼን ምንም ነገር ከሰማሁ ወራት ተቆጠሩ። **(starts to cry)** አሁን ደግሞ ይህ። ከአንቺ ጋ እዚህ ልቆይ እችላለሁ?

**26. KW END**

**27.** ትዕግስት: **(trying to comfort her)** አይዞሽ ምህረት። ሁሉም ነገር ደህና ይሆናል። አዎ እዚህ ከእኔ ጋ መቆየት ትችያለሽ። ቢያንስ ወላጆቼ እስኪመለሱ ድረስ። ቆይ አሁኑኑ ለዶክተር ዘሪሁን ልደውልላቸው…

**28. SFX: PRESSES MOBILE PHONE BUTTONS**

**29. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 2: ቅዱስ , ብሩክ AND አቶ ደንበል ARRIVE IN TANDIKA</u>**

**30. SFX: BUS STATION ATMO**

**31. SFX: TRUCK SLOWLY COMING TO HALT**

**32.** አቶ ደንበል: **(gently)** ቅዱስ , ብሩክ , ተነሱ ደርሰናል።

**33.** ብሩክ: **(getting up)** የት ነው ያለነው በጣም ደክሞኛል።…

**34.** ቅዱስ: **(yawns)** ወይኔ ይህን ቦታ አውቀዋለሁ። **(yells in delight)** ብሩክ ! - የአውቶቢስ ፌርማታው። እቤታችን ደርሰናል።

**35.** ብሩክ: **(disbelief)** ከምርህ ነው!!!

**36.** አቶ ደንበል: **(laughing along)** በሉ ልጆች… በጣም አዝናለሁ። እዚህ ጋ አወርዳችኋለሁ።

**37. SFX: TRUCK ENGINE BEING TURNED OFF**

**38.** ቅዱስ : ከእኛ ጋ መጥተው ወላጆቻችንን እና እህታችን ምህረትን አይተዋወቁም ?

**39.** አቶ ደንበል: ደስ ባለኝ ግን ጥሩ ሀሳብ አይመስለኝም። ከኪሳምባ ድረስ ሳመጣችሁ አደገኛ ውሳኔ ወስጄ ነበር። - እንዳትቀየሙኝ። ሁለታችሁንም ቀልቤ ወዷችኋል። ግን ላቦሪያ ውስጥ ስትሰሩ በእርግጥ ምን እንደተከሰተባችሁምንም የማውቀው ነገር የለም። ስለአክስታችሁም ቢሆን ማለት ነው። …. ስለዚህ የቤታችሁን መንገድ እና ያላችሁበትን እስካወቃችሁ ድረስ እዚህ ጋ ብትወርዱ ይሻላል።

**40.** ብሩክ: **(crying)** አቶ ደንበል! ስላደረጉልን ነገር በጣም እናመሰግናለን። በፍፁም አንረሳዎትም።

**41.** ቅዱስ: **(also weeping)** በፍፁም…

**42.** አቶ ደንበል: አታልቅሱ ልጆች - ሆነም ቀረ ወደዚህ መምጣቴ አይቀርም ነበር። ስለዚህ አያስጨንቃችሁ። ልረዳችሁ በመቻሌ ደስተኛ ነኝ። አንድ ቀን በድጋሚ እንደምንገናኝ እርግጠኛ ነኝ። አሁን ሂዱና ከቤተሰባችሁ ጋ ተቀላቀሉ።

**43. SFX: TRUCK DOOR OPENED**

**44. SFX: KIDS JUMPING OUT**

**45.** ብሩክ : ደህና ይሁኑ አቶ ደንበል። አንረሳዎትም።

**46.** አቶ ደንበል: ደህና ሁኑ ልጆች። ለወላጆቻችሁ ሰላምታዬን አቅርቡልኝ።

**47. SFX: TRUCK DOOR CLOSING, TRUCK ENGINE STARTING AND DRIVING OFF**

**48.** ቅዱስ : ቻውውው…

**49.** ብሩክ : ሄደዋል ቅዱስ። ና አሁን እማዬን አባዬን እና ምህረትን እናግኛቸው።

መንገዱን አስታውሰዋለሁ።

**50. MUSIC INTERLUDE (ALTERNATIVELY, CROSSFADE INTO NEXT SCENE)**

**SCENE 3: ወ/ሮ ሉሊት AND አቶ ሙላቱ ARRIVE IN THE CITY**

**51. BUS STOP ATMO, BUS TERMINAL WITH BUSES COMING AND GOING**

**52. SFX: BUS DOOR OPENS, PEOPLE GET OUT**

**53.** ወ/ሮ ሉሊት: **(exhausted)** አድካሚ መንገድ ነበር ሙላቱ ። በዛ ላይ ወደ ከተማ መመለስ የእንግድነት ስሜት ይፈጥራል። የገጠሩን ኑሮ ተለማምጄው ነበር።

**54.** አቶ ሙላቱ: ሉሊት ቆይ ሸክሙን ላግዝሽ። **(acts carrying heavy luggage)** ተመልሶ ወደዚህ መምጣቱ ጥሩ ሀሳብ አይመስለኝ።

**55.** ወ/ሮ ሉሊት: ሙላቱ ከወንጀሉ ጋ የሚያገናኝህ ምንም ነገር ከሌለ የሚያስፈራህ ነገር የለም።

**56.** አቶ ሙላቱ: ልክ ነሽ። ሉሊትዬ። ለማንኛውም ሁለታችንም ወደቤታችን ስለተመለስን ደስተኛ ነኝ። ከአሁን በኋላ ጥሩ ባል እንደምሆን ቃል እገባልሻለሁ።

**57.** ወ/ሮ ሉሊት: **(firmly)** እንዲሁም ጥሩ አባት ትሆናለህ፣ መጠጥም ማቆም አለብህ። ሙላቱ! ስራ መፈለግም አለብህ። ካለበለዚያ ምንም ዋጋ የለውም።

**58.** አቶ ሙላቱ: **(giving in)** ልክ ነሽ። ትክክል። -እሺ...

**59. SFX: BUS DRIVES PAST**

**60.** ቅዱስ : **(thrilled, shouting from far away)** ብሩክ ! ብሩክ ! ተመልከት... **(shouting)** እማዬ እማዬ!

**61.** ወ/ሮ ሉሊት: **(worried)** ሙላቱ ይሰማሀል?

**62.** አቶ ሙላቱ: ምን? እዚህ አውቶቢስ ማቆምያው አካባቢ ጫጫታው ምን አሰምቶን ብለሽ፤ የምትይውን በቅጡ መስማት አልችልም።

**63.** ብሩክ : **(excited, shouts)** እማዬ እና አባዬን አዛጋ ተመልከት።

**64.** ወ/ሮ ሉሊት: እንደሚመስለኝ የሰማሁት ሁለቱን… በፍፁም ይህ እውን ሊሆን አይችልም።

**65.** ብሩክ **and** ቅዱስ **together:** እማዬ!

**66.** ወ/ሮ ሉሊት: **(overwhelmed)** ውይ ውይ! ሙላቱ - እኔ አላምንም። ከመንገዱ ማዶ ተመልከት። ቅዱስ እና ብሩክ ፤ ልጆቻችን ናቸው የሚጠሩኝ!

**67.** አቶ ሙላቱ: **(dumbfounded)** ምን? የቱጋ? ...እውነትም እነሱ ናቸው! እኛውና!

**68. SFX:** ቅዱስ **AND** ብሩክ **RUN AFTER THEIR PARENTS**

**69. MUSIC INTERLUDE**

**<u>SCENE 4: ምህረት TAKES A PREGNANCY TEST</u>**

**70. SFX: NERVOUS FOOTSTEPS WALKING BACK AND FORTH**

**71.** ትዕግስት : **(reassuring)** ምህረት እረጋ በይ፤ ዶክተር ዘሪሁን በማንኛውም ደቂቃ እዚህ ይደርሳሉ።

**72. SFX: KNOCKING ON DOOR**

**73.** ምህረት: **(scared)** ወይ ፈጣሪ! ትዕግስት እኛ ናቸው አይደል ዶክተር ዘሪሁን። ምንድን ነው አሁን የማደርገው?

**74.** ትዕግስት : ሁሉንም ነገር እሳቸው ይነግሩሻል። ይግቡ ዶክተር

**75. SFX: DOOR OPENED**

**76. SFX: STEPS ዶክተር ዘሪሁን COMES IN**

**77.** ዶክተር ዘሪሁን: **(pleasantly)** እንደምን አለሽ ትዕግስት። አንቺ ምህረት መሆን አለብሽ? ዶክተር ዘሪሁን እባላለሁ። ትዕግስት ስላንቺ በስልክ ነግራኛለች። ወደ ውጭ ወጥተን ብቻችንን እንድንነጋገር ትፈልጊያለሽ?

**78.** ምህረት: አይ ምንም አይደል። **(trembling voice)** እኔ... ትዕግስት የትምህርት ቤት ጓደኛዬ ናት። ስለሁሉም ነገር ታውቃለች።

**79.** ዶክተር ዘሪሁን : ጥሩ። እንደዚህ ከሆነ... እርግዝሽ እንደው እንደምትጠራጠሪ ነግራኛለች።

**80.** ምህረት : እርግጠኛ አይደለሁም። ትዕግስት ነች እንደዛ ያለችኝ። እኔንጃ።

**81.** ዶክተር ዘሪሁን : አይዞሽ። ለዚህ ነው ወደዚህ የመጣሁት።

**82.** ምህረት : ምንድን ነው ማድረግ ያለብኝ ዶክተር ንገሩኝ...

**KW BEGIN**

**83.** ዶክተር ዘሪሁን : ጥሩ። በመጀመሪያ ማድረግ ያለብኝ የእርግዝና ምልዕክቶች እንዳሉሽ ማየት ነው።

**84.** ምህረት : ምልዕክቶች ሲሉ ምን ማለትዎ ነው? ምንም አይነት የህመም ስሜት የለኝም።

**85.** ዶክተር ዘሪሁን : የወር አበባሽ እንዳልመጣ ሰምቻለሁ። ግን ... የማጥወልወል ስሜት አለሽ?

**86.** ምህረት : የለም። ግራ ከመጋባት ውጪ እስካሁን የለኝም።

**87.** ዶክተር ዘሪሁን : ጡቶችሽ ከወትሮው ለስለስ ብለዋል?

**88.** ምህረት: **(shocked)** ምን? ይህ እርሶን አያገባዎትም።

**89.** ትዕግስት : ምህረት ! ዶክተር ለሚጠይሽ ጥያቄ ግልፅ መሆን አለብሽ። ርዳታ ለማግኘት ብቸኛው አማራጭ ይህ ነው።

**90.** ዶክተር ዘሪሁን : አይዞሽ ምህረት ። ይህን የምጠይቅሽ ለራስሽ ስል ነው። ይህንን ጥያቄ ማቅረብ ያለብኝ ስለ ሁሉም ነገር ለማረጋገጥ ነው።

**91.** ምህረት : እ… ምንም የተለየ ነገር አላስተዋልኩም።

**92.** ዶክተር ዘሪሁን : ድካምስ? ከቀድሞው የተለየ ይሰማሻል?

**93.** ምህረት: **(flatly)** አዎን! ድካም ሲሰማኝ ቆይቷል። ግን ቢሆንስ? ከጊዜ ወደ ጊዜ ሁሉም ተማሪዎች ይደክማቸዋል። የፈተና ወቅት ነው። ያስጨንቀናል። በዛ ላይ እቤት ውስጥ ብዙ ማገዝ አለብኝ።

**KW END**

**94.** ዶክተር ዘሪሁን **:** እሺ… እርግጠኛ እንድንሆን የእርግዝና ማረጋገጫ ምርመራ እናድርግ። ስለዚህ በጥንቃቄ አድምጪኝ። ወደ መፀዳጃ ቤት ሄደሽ ሽንት እንድታመጪልኝ። ከዛ በኋላ ጥቂት ደቂቃዎች ነው የሚወስደው። ከዛ የተሸከምሽው ነገር እንዳለ አለያም ዝም ብሎ ምልክት እንደሆነም በእርግጠኝነት እናውቃለን።

**95.** ምህረት: **(speaks to herself)** የተሸከምሽው ነገር ?ምን ህፃን ልጅ ማለታቸው ነው? መቼም እንደዛ እንደማይሆን ተስፋ አደርጋለሁ።

**96. MUSIC INTERLUDE**

## 97. <u>OUTRO - NARRATOR:</u>

**የ ምህረት የሽንት ናሙና ምርመራ ምን ያሳይ ይሆን? ቅዱስ እና ብሩክ አቤት ደርሰዋል። የአቶ ሙላቱ የቤተሰብ ቅልቅል ዘለቄታ ይኖረዋል? የሚቀጥለውን ክፍል ሰምታችሁ ድረሱበት። ይህንን ወይንም ከዚህ በፊት የተላለፉ ክፍሎችን ደግመው ለመስማት ከፈለጉ dw.de/lbe የተሰኘዉን ድረ- ገፃችንን ይጎብኙ፤ እዛው ድረገጻችንላይ የዳንኤል የቪዲዮ ዘገባንም ያገኛሉ። ስለ በማድመጥ መማር ማንኛውም ዜና እንዳያመልጥዎ የፌስቡክ ገፃችንን ጎብኙ። ለዛሬ ያልነው የእስካሁኑ ነበር። ደህና ሁኑ።**